

# THRIVE MONTGOMERY 2050: ቀጣይ ዕድላችንን አብረን እናቅድ

## Thrive Montgomery ምንድን ነው?

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ለመኖር፣ ለመስራት፣ ለመገናኘትና ለመጫወት ምቹ የሆነ ምርጥ ቦታ ነው። እንደዚህ ሊሆን የቻለው ግን በአጋጣሚ አይደለም። ከአስርት ዓመታት በፊት፣ በ *On Wedges and Corridors* 1964 አጠቃላይ ዕቅድ አማካይነት፣ ፕላነሮችና የማህበረሰብ አባላት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ድንቅ ማህበረሰቦች፣ ቦታዎችና አካባቢዎችን ቅርጽ አስተካክለዋል።

ይህ Thrive Montgomery 2050 የተባለው ማሻሻያ አዳዲስ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ማለማመድ፣ ታሪካዊ የፍትሐዊነት እጦትን መቅረፍና ካውንቲው እንዴት ማደግ እንዳለበት የምናስብበትን መንገድ መቀየር ላይ ያተኮረ ነው። Thrive Montgomery 2050 ይበልጥ ከተሜ የሆነ፣ ይበልጥ ብዝሃነት የሰፈነበትና ይበልጥ የተሳሰረ ካውንቲ የመፍጠር ራዕይ አለው። የ Thrive Montgomery 2050 ውጤት ውሳኔ አሰጣጥን የሚመራና ሞንትጎመሪ ካውንቲ ሁሉም ሰው ስኬታማ የሚሆንበት፣ ተጨማሪ ዕድሎች የሚያገኙበትና ባማረና ለሁኔታዎች በማይበገር አካባቢ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው ሕይወት የሚኖርበት ቦታ መሆኑን ለማረጋገጥ ሐብቶችን ለማግኘት የሚያስችል ዕቅድ ነው። የ Thrive Montgomery 2050 ዓላማ እስከ 2050 እና ከዚያ በኋላ ሞቅ ደመቅ ያለ ኢኮኖሚ፣ ለሁሉም ነዋሪዎች ርቱዓዊነትና ጤናማ አካባቢ መኖሩን ማረጋገጥ ነው።

# ዒላማ – ሶስት ዋና ዋና ውጤቶች

### ኢኮኖሚያዊ ጤና

ዋና ዋና የስራ ቀጣሪዎችን በመሳብና ጠብቆ በማቆየት፣ የፌዴራል ካምፓሶቻችንን በቀጣይነት በማጎልበት፣ አነስተኛ የንግድ ስራዎችን እና አዲስ ግኝትን በመደገፍና ከፍተኛ ጥራትና ብዝሃነት ያለው የሰራተኛ ሐይል ጠብቆ በማቆየት ኢኮኖሚው ሞቅ ደመቅ ያለ፣ ጠንካራና ተወዳዳሪ መሆኑን ለማረጋገጥ እንፈልጋለን።

### ፍትሃዊነት

ሁሉም ነዋሪዎች ሊደረስበት የሚችል መኖሪያ ቤት፣ ጤናማ ምግብ፣ የስራ ቅጥር፣ ትራንስፖርት፣ ትምህርትና ሌሎች ነገሮችን በእኩልነት የሚያገኙበት ቦታ ለመፍጠር እንፈልጋለን።

### አካባቢዊ አይበገሬነት

የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋትና የታቀዱ ለውጦችና ያልተጠበቁ ክስተቶች የሚያስከትሉትን ተጽእኖ ለማቃለልና የተፈጥሮ ሐብቶቻችንን ጠብቆ ለማቆየት ምርጥ የሚባሉ ስትራቴጂዎችን መጠቀም አለብን።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የኮሪደሮች መረብ



### የዕቅዱ ራዕይ

የ Thrive Montgomery 2050 ራዕይ ይበልጥ ከተሜ የሆነ፣ ይበልጥ ብዝሃነት የሰፈነበትና ይበልጥ የተሳሰረ፣ እንደዚሁም ለነባር ነዋሪዎቹ ከፍተኛ ጥራት ያለው ኑሮ እንዲኖሩ በማስቻል አዳዲስ ነዋሪዎችና አዳዲስ ሃሳቦችን የሚያስተናግድ ካውንቲ መፍጠር ነው። በተለይም፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲ በ2050 ሞቅ ደመቅ ባሉ ኮሪደሮች የተሳሰሩ የተሟሉ ማህበረሰቦችን መረብ ያቀፈ ነው። ግለሰባዊና የተለዩ የአጎራባች አካባቢ ተግባር ማዕከላትና የከተማ ማዕከላት የተለያዩ የቤት ዓይነቶችና የዋጋ ደረጃዎችን በማቅረብ የመሬት አጠቃቀምን ያሳድጋሉ። መኖሪያ ቤት ከትራንዚት፣ ከስራ ቦታዎች፣ ከአስፈላጊ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ ከሕዝባዊ መዝናኛ ቦታዎችና በንቃት ከሚሰሩ የፓርክ ቦታዎች አቅራቢያ ይገኛል። እነዚህን የተሟሉ ማህበረሰቦች ከቀሪው የካውንቲው ክፍል ጋር የሚያስተሳስሩ ሁለት ዓይነት ኮሪደሮች አሉ፡ 1. መልቲሞዳል ትራንስፖርትና አገልግሎቶች፤ እና 2. አረንጓዴ ፓርኮች፣ የጅረት ሸለቆዎችና ወራጅ ውሃ

# መሰረታዊ ሃሳቦች

መሰረታዊ ሃሳቦች የመነጩት በማህበረሰብ ጭውውቶች፣ በኤክስፐርት ቃለ መጠይቆች፣ ትንተና እና ጥናት አማካይነተ ነው። የ Thrive Montgomery 2050 ዕቅድ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የተጋረጡበትን ተግዳሮቶች የሚዳስስ ሲሆን ከእነዚህ መሰረታዊ ሃሳቦች ጋር በተያያዙ ተከታታይ ግቦች፣ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች አማካይነትም የዕድገት ዕቅዶችን ያካትታል።


## ዋና ዋና ገፅታዎች




የ Thrive Montgomery 2050 ምክረ ሃሳቦች ዘጠኝ መሰረታዊ ገጽታዎችን ያካትታሉ። እነዚህ ገጽታዎች በሙሉ ከሶስቱ የኢኮኖሚያዊ ጤና፣ ርቱዓዊነትና የአካባቢ አይበገሬነት ውጤቶች ጋር የተያያዙ ናቸው።

## 1. የተሟሉ ማህበረሰቦችን መፍጠር

የተሟሉ ማህበረሰቦች ማለት ሁሉም ሰው ሊኖርባቸው፣ ሊሰራባቸው፣ ሊገበያይባቸው፣ ሊማርባቸውና ሊጫወትባቸው የሚችሉ ቦታዎች ናቸው። የተሟሉ ማህበረሰቦች የእግር ጉዞ ለማድረግ ቀላል ናቸው፣ እንደ ፓርኮችና አብያተ መጻሕፍት ያሉ መዝናኛ እና መሰባሰቢያ ቦታዎችን ያቀርባሉ፣ ሰዎችም ዕለታዊ አስፈላጊ ነገሮቻቸውን ከቤታቸው አቅራቢያ እንዲያገኙ ያስችላሉ። የተሟሉ ማህበረሰቦች በካውንቲው የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የሚለያዩ ሲሆን ከተሜ፣ ከፊል ከተሜና ገጠራዊ አውዶችንም ያንጸባርቃሉ። የተሟላ ማህበረሰብ በዘር፣ በብሔርና በኢኮኖሚ ረገድ ብዝሃነት የሰፈነበት ሲሆን፣ በእግር፣ በብስክሌት ወይም በትራንዚት የሚደረስባቸውን የተለያዩ የቤት ዓይነቶች፣ አጠቃቀሞች፣ መዝናኛዎችና አገልግሎቶችንም ያካትታል። የልማትና የከተሜነት ጥቅል መልክ የተሟሉ ማህበረሰቦችን ለመፍጠር ወሳኝ ነው። Thrive Montgomery 2050 የ15 ደቂቃ ኑሮ በማለት ይጠራዋል። ግቡም፣ በሁሉም መንገድ ብዝሃነት የሰፈነባቸውና በ15 ደቂቃ የእግር ጉዞ፣ የብስክሌት ግልቢያ ወይም ትራንዚት ርቀት ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማቅረብ የሚችሉ የተሟሉ ማህበረሰቦችን መፍጠር ነው። ይበልጥ የተቀራረበ ልማት ትራንዚት፣ የእግር ጉዞና የብስክሌት ግልቢያ ዋነኛ የትራንስፖርት ዘዴዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ ሲሆን፣ ንቁ የአኗኗር ዘይቤዎችና ማህበራዊ ትስስሮችን ለማምጣት የሚደረጉ ጥረቶችን ያጎለብታል። የተሟሉ ማህበረሰቦች ጽንሰ ሃሳብ የተለያዩ የቤት አማራጮችን የሚያካትት ሲሆን ይህ ደግሞ ይበልጥ ዋጋቸው ተመጣጣኝና ምቹ የሆኑ ቤቶችን ለማግኘት እንደዚሁም በዘርና ማህበረ-ኢኮኖሚ ረገድ ብዝሃነት የሰፈነባቸው አጎራባች አካባቢዎች እንዲፈጠሩ የሚያደርግ ነው። Thrive Montgomery 2050፣ የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ከማድረግ ባሻገር ማህበራዊ ትስስሮችን የሚያዳብሩ፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን የሚያበረታቱና ሞቅ ደመቅ ያሉ ማህበረሰቦችን ለመፍጠር የሚያግዙ ፓርኮችና ሕዝባዊ ቦታዎችን ዲዛይን እንዲደረጉ ሃሳብ ያቀርባል።




## 2. የዘር ፍትሃዊነትና እኩልነትን ማሳካት

በ Thrive Montgomery 2050 ውስጥ ያሉ ምክረ ሃሳቦች በካውንቲው ውስጥ የባህል ብዝሃነትን ማከልና ብዝሃነት የሰፈነባቸውና አካታች ማህበረሰቦችን የሚመርጡ የንግድ ድርጅቶችና ነዋሪዎችን በመሳብ የሃገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ማሳደግ የሚሹ ናቸው። ካውንቲው የሐብት ውስንነት ችግር ያለበት ከመሆኑ አንጻር፣ ነጭ ያልሆኑ ነባርና አዳዲስ ማህበረሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት፣ የስራ ስልጠና እና ሌሎች ዕድሎችን የመሳሰሉ አገልግሎቶችና ኢንቨስትመንቶች ላይ ተመጣጣኝ ድርሻ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለብን። የርቱዓዊነት ችግርና የዘር ልዩነትን መፍታት የሚቻለው እኛ ሁላችንም የተሳሰርን ስለመሆናችንና ወደ ቀጣይ ሁኔታ እንዴት እንደምናድግ የጋራ ጥቅም የምንጋራ ስለመሆናችን የጋራ ግንዛቤ መያዝን ይጠይቃል።

## 3. ለሁሉም ሰው ሊደረስበት የሚችል መኖሪያ ቤት ማቅረብ

ሞንትጎመሪ ካውንቲ በተለይ ዋጋቸው ተመጣጣኝና የገበያ ዋጋን መሰረት ያደረጉ በቂ ቤቶችን እያቀረበ አይደለም። እስከ 2045 ድረስ ወደ ካውንቲው መጥተው ይኖራሉ ተብለው ለሚገመቱ 200,000 አዳዲስ ነዋሪዎች በቂ በሆነ መጠን የቤት አቅርቦታችንን ካላሳደግን፣ ነባሮቹ ማህበረሰቦቻችን ውድነታቸው ይጨምራል፣ ብዝሃነታቸውና ትስስራቸው ይቀንሳል፤ የሰለጠነ የሰው ሐይል ለመሳብና ይዞ ለማቆየትም አስቸጋሪ ይሆናል። ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ሲነጻጸር፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ያለው የኑሮ ውድነት የሚጨምረው በዋነኛነት በቤት ዋጋ ምክንያት ነው፤ በዚህም ምክንያት ሰራተኞችን መሳብና ይዞ ማቆየት ስለሚያስቸግር ቀጣሪዎችንም መሳብ/ይዞ ማቆየት አስቸጋሪ ይሆናል። በተጨማሪም፣ በዘርና በመደብ ላይ የተመሰረተው የዘረኝነትና ሆን ተብሎ የሚፈጸም ልዩነት አሻራ እንደ ስራዎችና ትምህርት ቤቶች የመሳሰሉ ዕድሎችና ሐብቶች መልክዓ ምድራዊ ክፍፍል ላይ ቀጣይነት ያለው ተጽእኖ ያሳድራል፤ ይህ ደግሞ የቤቶችን አቅርቦትና ብዝሃነት ለዕድሎች ውህደትና ርቱዓዊነት ወሳኝ ያደርገዋል። በዋጋ ተመጣጣኝነት/ተደራሽነት ላይ የሚታየውን ክፍተት በዘላቂነት ለመቅረፍ ብቸኛው መንገድ አቅርቦትን ማሳደግ በመሆኑ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን ተጨማሪ ቤቶች መገንባትና ጠብቆ ማቆየት ያስፈልገናል።




## 4. ራሳቸውን የቻሉ ቤቶች ያሉባቸው መኖሪያ አካባቢዎች በትራንዚት አቅራቢያ እንዲሰሩ ዳግም ማሰብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰቦች ከቤት፣ ከዋጋ ተመጣጣኝነት፣ ከቤት ስፋትና ዓይነት እንደዚሁም ለትራንዚት ካለው ቅርበት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ፍላጎቶች አሏቸው። ካውንቲው ቀጣይነት ያለው የቤቶች አቅርቦት ክፍተትም አለበት። የ Thrive Montgomery 2050 ዓላማ ራሳቸውን የቻሉ ቤቶች ብቻ የሚገኙበት ቀጠና በስራ ቅጥር ማዕከላትና ትራንዚት አቅራቢያ ባሉ አጎራባች አካባቢዎች የልማት እንቅፋት አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው። በነባር ራሳቸውን የቻሉ ቤቶች ቀጠና ውስጥ ጨምሮ በትራንዚት አቅራቢያ የተለያዩ ዓይነት ቤቶችን ግንባታ የሚደግፉ ፖሊሲዎችና እርምጃዎች በዕቅዱ ውስጥ ይካተታሉ። ይህም ከዚህ በፊት ከመኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ የነበሩ የርቱአዊነት ጉድለቶችን ካውንቲው ለመፍታት የሚጀምርበት ወሳኝ ሒደት ነው፤ በሁሉም የገቢ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ነባርና ቀጣይ ነዋሪዎች ተጨማሪ የቤት አማራጮችንም ይፈጥራል። በተለይም፣ Thrive Montgomery 2050 ከፍተኛ አቅም ካለው ትራንዚት አቅራቢያ በሚገኙና በአሁኑ ጊዜ ራሳቸውን ለቻሉ ቤቶች ብቻ በተከለሉ ቀጠናዎች የተወሰነ መጠን ያለው የሰዎች ጥግግት ጭማሪ እንዲደረግ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ይህም እንደ ባለ ሁለት አፓርታማ፣ ባለ ሶስት አፓርታማና ባለ አራት አፓርታማ ቤቶች፣ ባለ ሶስት አፓርታማ ቤቶችና ባለ አራት አፓርታማ ቤቶችን ለተለያዩ የቤተሰብ ፍላጎቶችና የዋጋ ተመጣጣኝነት ደረጃዎች ያቀርባል።



## 5. ከመኪኖች ይልቅ ለሰዎች እቅድ ማውጣት

ለሰዎች ዕቅድ ማውጣት ማለት የመተላለፊያ መንገዶች፣ የእግረኛ መንገዶችና ሌሎች የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን ለእግረኞች፣ ለብስክሌተኞች፣ ለትራንዚት ተጠቃሚዎች ወይም ለባለመኪኖች አስተማማኝ በሆነ መልኩ ዲዛይን ማድረግ ማለት ነው።  ካውንቲው በአሁኑ ጊዜ በዋነኛነት መኪኖችን በፍጥነት ለማንቀሳቀስ ተብለው ዲዛይን የተደረጉ በርካታ መንገዶች አሉት። ይህም ትኩረት ሰዎች ሌላ አማራጭ ከሌላቸው በስተቀር የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ብስክሌት መጋለብ ወይም ትራንዚት መጠቀምን የማያበረታቱና ደህንነታቸው ያልተጠበቀ የመተላለፊያ መንገዶች እንዲኖሩ ያደረገ ነበር። Thrive Montgomery 2050 የሰነቀው ዳግም ራዕይ እነዚህ ዋና ዋና የመተላለፊያ መንገዶች ፈጣንና አስተማማኝ ትራንዚትን የሚደግፉ፤ ምቹ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀና አስተማማኝ የስራ ቦታዎችን የሚደግፉና ማራኪ ኪነ- ሕንጻ እና  የጎዳና ገጽታዎችን የሚያሳዩ ኮሪደሮች ማድረግ ነው። ነዋሪዎችና ሰራተኞች ከአገልግሎቶችና ስራዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ የሚያስተሳስሯቸው ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የጉዞ ምርጫዎችን ማቅረብ በመኪናዎች ላይ የሚኖር ጥገኝነትን በመቀነስ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ተገቢና በአካባቢ ረገድ ዘላቂነት ያለው የትራንስፖርት ስርዓት ለመፍጠር ያግዛል። ይህ ማለትም ሰዎችን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴን ለመደገፍና የፈጣን አውቶብስ ትራንዚት እና የፐርፕል መስመርን በመጠቀም ከዕድልና ተግባር ማዕከላት ጋር ለማስተሳሰር የእግረኛ መንገዶችና የብስክሌት መንገዶችን ማቀድ ማለት ነው።



## 6. የበካይ ጋዝ ልቀትን ማስወገድ

ከ Thrive Montgomery ግቦች መካከል አንደኛው “የበካይ ጋዝ ልቀቶችና አደገኛ በካይ ነገሮችን ከትራንስፖርት ስርዓት ማስወገድ” ነው። ዕቅዱ ተሽከርካሪ በሚበዛባቸው ሰዓታት ለሚንቀሳቀሱ መኪኖች ክፍያ ማስከፈልና ለአዲስ ልማት የመኪና ማቆሚያ መስፈሮችን በመቀነስ የአውቶሞቢል ጉዞን አለማበረታታት፤ ለእግር ጉዞ፣ ለብስክሌት መጋለቢያና ለትራንዚት የሚሆኑ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ኔትወርኮች በማቅረብ መኪና የማይነዱ አካላትን ማበረታታት፤ እና የኤሌክትሪክ መኪኖች በብዛት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎች ይመቻቹ ዘንድ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል። በ2015፣ የሞንትጎመሪ ካውንት የበካይ ጋዝ ልቀት ውስጥ ትራንስፖርት የ41% ድርሻ ነበረው፤ የመኖሪያና የንግድ አገልግሎት ሕንጻዎች በጋራ ከሚያመነጩት 51 በመቶ በመቀጠል የተመዘገበ ነበር። የሕዝባዊ ትራንዚት አጠቃቀምን በማሳደግ የግል ተሽከርካሪዎች የሚሸፍኑትን የጉዞ ርቀት መቀነስ ከትራንስፖርት ጋር የተያያዘውን የበካይ ጋዝ ልቀት ለማስቀረት የተሻለው መንገድ ነው። ሰፋ ያለ የቤት ዓይነቶች መኖራቸው የኢነርጂ ፍጆታንና የበካይ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ በተለይም አነስተኛ ክፍሎች ያላቸው፣ የጋራ ግድግዳ ያላቸውና በብስክሌት ወይም በእግር ጉዞ ሊደረስባቸው የሚችሉ የተለያዩ መዳረሻዎች አቅራቢያ ላይ የሚገኙ ከአንድ በላይ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ሕንጻዎች።

## 7. የቦታን ምርጥ ዲዛይንና ጠቀሜታን ማስቀደም

ዕቅድ ማውጣት ማለት በሕዝባዊ መስክና በአዲስ የግል ልማት ውስጥ አዳጊ ማህበረሰቦችን መፍጠርና ታላላቅ ቦታዎችን ማጎልበት ማለት ነው። ምርጥ የሆነ ዲዛይን ተግባቦትና ማህበራዊ ትስስርን በማቀላጠፍ/በማበረታት ረገድ ተግባራዊ ዓላማዎችን ያስፈጽማል። ለጥበብና ለባህል የሚደረግ ድጋፍ ኩራትና የቦታ ስሜትን ያጠናክራል፣ ብዝሃነት ዋጋ እንዳለው በተግባር ያሳያል፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲም ሁሉም ሰው ቤቴ ብሎ እንዲጠራው ይበልጥ አስደሳችና ማራኪ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህ ማለትም የዲዛይን መመሪያዎች፣ የዲዛይን አማካሪ ፓናሎች፣ የዲዛይን ውድድሮችና ሌሎች መሳሪያዎችን በመጠቀም ለሁሉም ሕዝባዊና የግል ኪነ ሕንጻ፣ መሰረተ ልማትና ክፍት ቦታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ጥራት ያለው ዲዛይን ማዘጋጀት ማለት ነው።



## 8. ኮሪደሮችን የአዲስ ዕድገት ቦታ ማድረግ

ዕድገት በመሙያ ቦታና በልማት አማካይነት በኮሪደሮች አቅጣጫ ማተኮር አለበት። ይህ ትኩረት የተደረገበት ልማት ለእግር ጉዞ የሚያመቹና ሞቅ ደመቅ ያሉ ቦታዎችን ለመፍጠር የተለያዩ አገልግሎቶችን ቅይጥ የሚደግፉ የተግባር ማዕከላትን የማቋቋም አቅም ይፈጥራል፤ ይህ ደግሞ ለኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ወሳኝ ነው። ሁሉንም የዕድገት ዕቅድ በነባርና በታቀዱ የባቡርና የአውቶብስ ፈጣን ትራንዚት ኮሪደሮች አቅጣጫ ማሰባሰብ እነዚህ ደህንነታቸው ያልተጠበቀ የትራፊክ አውራ መንገዶች የተለያዩ የንግድ አገልግሎቶች የሚሰጡና የተለያዩ የመኖሪያ ዓይነቶች ደህንነታቸው የተጠበቁና ማራኪ አገናኞች ሆነው እንዲቀየሩ ያመቻቻል። በእነዚህ ኮሪደሮች አቅጣጫ የሚኖር ዕድገትን ለመደገፍ፣ ባለ ሁለት አፓርታማ፣ ባለ ሶስት አፓርታማ፣ ታውን ሃውሶች፣ ለመኖሪያና ለስራ የሚውሉ ቤቶችና አነስተኛ ባለ ብዙ ቤተሰብ መዋቅሮችን የመሳሰሉ የተለያዩ የቤት ዓይነቶችን በማስተዋወቅ አሁን ባሉት ራሳቸውን የቻሉ መኖሪያ አካባቢዎች ላይ ለውጥ ማድረግን ይጠይቃል። ይህ አቀራረብ ቦታን አስፋፍቶ መጠቀምን በማስቀረትና ዕድገትን ይበልጥ አካባቢያዊ ዘላቂ እንዲሆን በማድረግ የግብርና መጠባበቂያን ይጠብቃል፣ የመንገዶችን ወጪ ይቀንሳል፣ የትራንዚትን ወጪ ቆጣቢነት ያሳድጋል።

## 9. ክልላዊ መፍትሔዎችን ማመንጨት

ወደ 40% የሚሆኑት የካውንቲው ነዋሪዎች በዋሽንግተን ዲሲ፣ ሰሜናዊ ቨርጂኒያ እና በሌሎች የቨርጂኒያ አካባቢዎች በሚገኙ እንደ Fort Detrick፣ Fort Meade፣ Columbia፣ Frederick፣ College Park እና Baltimore ባሉ ዋና ዋና የስራ ቅጥር ማዕከላት ውስጥ ተቀጥረው ይሰራሉ። ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት እጥረት፣ ኢኮኖሚያዊ ፉክክር፣ ትራንስፖርት እና የአየር ንብረት ለውጥን የመሳሰሉ ጉዳዮች ክልላዊ መፍትሔዎችና ስትራቴጂዎች ያስፈልጋቸዋል። ለሁሉም ተግዳሮቶች ክልላዊ መፍትሔዎችን ታሳቢ ማድረግ ያለብን ሲሆን፣ ሞንትጎመሪ ካውንቲንም የታላቁ ስርዓተ ምሕዳር አንድ አካል አድርገን ማሰብ አለብን። እነዚህን ጉዳዮች በመላው ዋሽንግተን ዲሲ እና ባልቲሞር ሜትሮ አካባቢዎች ካሉ ጎረቤቶቻችን ጋር ስለምንጋራ መፍትሔውንም መፈለግ ያለብን በጋራ ነው።

## Thrive Montgomery 2050 የሚተገበረው እንዴት ነው?

Thrive Montgomery 2050 የትኛውንም የቀጠና አመዳደብ ወይም ሌሎች ደንቦችን ወዲያውኑ አይቀይርም። የፖሊሲዎቹና እርምጃዎቹ ትግበራ በቀጣዮቹ አስርት ዓመታት ውስጥ በሚኖሩ የተለያዩ መሳሪያዎች ላይ ይመሰረታል። Thrive Montgomery 2050 በቀጣዮቹ ዓመታት ውስጥ ለሚኖሩ ለአዳዲስ ማስተር፣ የዘርፍና ተግባራዊ ዕቅዶችና ዝርዝር ጥናቶች  የሞንትጎመሪ የዕቅድ ማውጣት ስራ ፕሮግራም ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፤ የግል ልማትን ዲዛይን እና የቁጥጥር ክለሳ ቅርጽ ያስይዛል፤ የፕላን አውጭ ቦርዱን ውሳኔ አሰጣጥም ይመራል።  ይሁን እንጂ፣ የThrive Montgomery ቅርበትና ተጽእኖ ከመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅት የሚያልፍ ነው። የThrive Montgomery አመራርም የተለያዩ የካውንቲ እና ክልላዊ ኤጀንሲዎች የመሰረተ ልማት፣ የፋሲሊቲ፣ የሪል እስቴትና ሌሎች ዕቅድ ዝግጅቶች ላይም ተጽእኖ እንዲያሳድር የታሰበ ነው።

| የአጭር ጊዜ እርምጃዎች | የመካከለኛ ጊዜ እርምጃዎች | የረዥም ጊዜ እርምጃዎች |
|---|---|---|
| **እስከ 5 ዓመት ድረስ**<br>ትግበራን በፍጥነት ለማስጀመር ከፍተኛ ቀዳሚነት የሚሰጣቸው | **ከ6 እስከ 15 ዓመት**<br>የአጭር ጊዜ እርምጃዎችን ይከተሉ፤ ለመተግበር ተጨማሪ ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ | **ከ16 ዓመት በላይ**<br>ተጨማሪ፣ የአጭር ጊዜና የመካከለኛ ጊዜ አጋዥ ስራን ሊጠይቅ ይችላል |



## ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀጣይ እጣ ፈንታ ዕቅድ ዝግጅት ውስጥ ይሳተፉ


**ኢሜይል:** thrive2050@montgomeryplanning.org

**ያናግሩ: የፕሮጀክት ሃላፊ** Khalid Afzal, 301-495-4650

**ተጨማሪ መረጃ ያግኙ:** ThriveMontgomery.com **ወይም** MontgomeryProspera.com